## አዲስ አበባ-ጎርፍ ብዙ ሺሕ ሕዝብ አፈናቀለ | 07.09.2010 | 14:00 UTC DW

ሰሜናዊ-ምሥራቅ ኢትዮጵያን ያጥለቀለቀው ጎርፍ አስራ-ስድስት ሺሕ ያሕል ሕዝብ ማፈናቀሉን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አስታወቀ፣የድርጅቱ የሠብአዊ ርዳታ ማስተባበሪያ ቢሮ (OCHA) እንዳስታወቀው ባለፈው ነሐሴ ሃያ-አንድ፤አፋር መስተዳድር የሚፈሰው የሎጊያ ወንዝ ገደፉን አልፎ በመፍሰሱና የትንዳሆ ግድብ በመደርመሱ አካባቢው በውሐ ሙላት ተጥለቅልቋል፣ጎርፉ ካፈናቀለው ሕዝብ በተጨማሪ ግምቱ በውል ያልታወቀ ሰብልና ንብረት አበላሽቷል፣መንገዶችንና ድልድዮችንም አፈራርሷል፣የኦቻ ዘገባ በሰው ሕይወት ላይ የደረሰ ጉዳት ሥለ-መኖር አለመኖሩ ግን ያለው ነገር የለም፣ባለፈው ሐምሌ ማብቂያ በማዕከAላዊ አማራ መስተዳድር የጣለው ሐይለኛ ዝናብ አስራ-አንድ ሺሕ ሕዝብ ሲያፈናቀል፤በአካባቢው የደረሰ ርዕደ-ምድር ደግሞ አስራ-ዘጠኝ ሰው ገድሎ ነበር፣ ዘንድሮ ኢትዮጵያ ውስጥ የጣለና የሚጥለው ዝናብ ከሰወስት መቶ-ሺሕ በላይ ሕዝብ ሊጎዳ እንደሚችል አለም አቀፉ ድርጅት እያስጠነቀቀ ነው፣